# <u>የጥቅል መንግሥት በኢትዮጵያ</u>
# <u>ንድፈ-ሃሳብ ለውይይት፤</u>

**<u>በአቤ ኮስትሬ</u>**

<u>ኢትዮጵያ የጥቂቶች ሳትሆን የብዙሃን መሆኗን</u>
<u>ለማሳየት በአንድ ልቦና እንነሳ !!</u>

## <u>ለመግቢያ ያህል በጣም ያረካኝን ከመጽሐፈ-ዴርቶጋዳ- የአባ ዝንበሩን መልዕክት ከታች በሁለት መስመሮች ልጥቀስ !-</u>

**<u>-እያወቅህ ስትመጣ በድንቁርና የታወሩ ዓይኖችህ</u>**
**<u>ሲገለጡልህ የበለጠ መበዝበዝህ ይሰማሃል !!!</u>**

**<u>-መብትህን ካላወቅህ መጨቆንህ አይገባህም !!!</u>**

ያም የፖለቲካ አዋቂና ምሁር ነኝ ይበል ! ያም ስለ ዲሞክራሲ አካሄ
ድና ምሥረታው አዋቂው እኔ ነኝ ይበል ! ያም የዘርና ሃይማኖትን ጉዳይ
በተመለከተ አዋቂውና መፍትሔውን ላቀርብ የምችል እኔው ነኝ ይበል !
ነገር ግን በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ለሕዝብ መፍትሔ የሰጠ የፖለቲካ
ድርጅትም ሆነ የዘር ድርጅት እንደሌለ ፤ ለዘመናት ያሳለፍነው ታሪክ
ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል ። በዚህ ጉዳይ ወደኋላ ተመልሰን ከርክር
ውስጥ አንገባም የሚል አቋም አለን ።

በመሆኑም በየዘመናቱ የተፈጠረውንና ትውልድ የፈጀውን !! የሀገርን ሀብት
አሟጦ የበላውን ፤ የሰው ልጆችን ጎሊና አቁስሎ መጥፎ ታሪከ መዘክርን እያስ
መዘገበ ያለውን ፤ እኛው በኛው የተቋሰልንበትን ፤ ያለምንም ፋይዳ የተላለቅን
በትን ደካማ አስተሳሰብና ፤ ሕዝባዊ አመለካከት ያልነበረውን ሥርዓት ዛሬውኑ
ከላያችን አውልቀን መጣል ይኖርብናል ። አሁን ደግሞ እርስ በርስ ከመቃረን
እንዲሁም ከጥላቻና ጀብደኝነት ፤ ስሜታዊነት ነፃ የሚያደርገንን ፤ ከዘመኑ የዓ
ለማት ሕዝብ ጋር የሚያቀራርበንን ሌላ አመለካከት ለመፍጠር ተገደናል ።
ማለቴ የዚህ ንድፈ-ሃሳብ አቅራቢዎች ።

ይህ አዲሱ ራዕያዊ አስተሳሰብ እንደ ቀድሞው ያስተላልቀናል ? ወይስ ያፋቅ
ረናል ? ብሎ መንገዱን መዳሰስና መወሰን የዚህ ትውልድ ውሳኔ ቢሆንም አዲሱ
ንድፈ-ሃሳብ ወደ ትክክለኛው የአዕምሯዊ እሳቤና ውጤቱ ፤ እንዲሁም ከሠለጠ
ነው ዓለም ጎራ የሚከተን እንጂ ፤ ምንም ዓይነት ጎጂነት እንደሌለው የዚህ
ንድፈ-ሃሳብ አቅራቢዎች አፍ ሞልተን የምንናገረውና ፤ ያለመጠራጠር ከልብ
የምናምንበት ነው ። በርግጥ ይህን ሃሳብ ለሕዝባችን ስናቀርብ አንድ የተሰማን
ነገር እንዳለና አሁንም ያንን መደበቅ እንደማንችል በእርግጠኝነት እናስቀምጠ
ዋለን ። ይኸውም ፡-

በታሪካችን ውስጥ ተዋልደናል ! ዘረ ብዙ ሕዝቦች ሆነናል ፤ በአኩሪ ባኅልና
በቋንቋችን በልጽገናል ! በአፍሪካ ብቸኛ ባደረገን ፊደላችን በዓለም የተለየ ክብር
ተጎናጽፈናል ! ወዘተ....በድንቅ ታሪካችን ጭምር ኮርተናል ። ከኛ በሥልጣኔ
በቀደሙ ኃይላት ጥቅም አነፍናፊነትና ፤ ውስጣችንም በበቀሉ አረሞች የተነሳ
በመካከላችን ፤ ዘር-ሃይማኖትና ቋንቋን ተንተርሠው ቅራኔ እንዲፈጠር ቢያደር
ጉብንም ፤ የራሳችንን መሪዎች ራሳችን መርጠን ሥልጣነ-መንግሥት ልናስጨ
ብጥ እንዳንችል ባደረጉት መፍጨርጨር የዲክታተር አገዛዝን በላያችን ቢያንጹ
ብንም ፤ ሕዝባችን ግን ያንን ሁሉ ውዥንብር ተቋቁሞ በዘር ሃይማኖት ምክን
ያት ሳይወናበድ ነፃነቱን ፤ ፍቅርና ሰላሙን ፤ ባኅሉን ጠብቆ መኖሩን ፤ ''እንኳ
ንስ እኛ ግመልና እህያዎቻችን ባንዲራችንን ያውቃሉ !! '' እስከሚባል ድረስ
የሀገር ኩራትና አንድነት የተሰማን ሕዝብ ነን ። በዚህም ሳናበቃ የመጣውን
ጠላት ሁሉ አንበርክከንና አሳፍረን መመለሳችንን ታሪከ መዘክር አይዋሽም ።

ታዲያ የዘመናት ችግራችን ምንጩ ምንድነው ? ይህንንስ ለማስወገድ ምን
ማድረግ ይኖርብናል ? ከሚል ጥያቄ ተነስተን ከላይ ርዕስ ያደረግነውን የጥቅል
መንግሥት አዲስ ሥርዓትን አገኘን !! ለዚህስ አዲስ ሥርዓተ-መስተዳድር ምን
ያስፈልገዋል ? ምንስ የማይመቸው ሁኔታ ይኖራል ? እንዴትስ እናመቻቸዋ
ለን ? የተሰኙ ሃሳቦች ሳያስጨንቁን አልቀሩም ።

ሀ / ይህስ አዲስ ሥርዓት ምን ያስፈልገዋል ?

ለ / አዲሱን ሥርዓት ከመቀበል አኳያ ፤ ከኛስ ደካማ ጎን ማስ ወገድ የሚገባን ምንድነው ?

ሐ/ ምን ዓይነት ኅብረተ-ሰብ ነው ያለን ? ሕዝቡ የሚፈልገ ውስ ሥርዓተ መስተዳድር ምን ዓይነት ይሆን ? ለሚለው ጥያቄ ግን ካሁን ቀደም በግልጽ ይህን ይመስላል ተብሎ ባለመቅረቡና ፤ የራሱ ባልሆነ የኮምዩኒዝምንና ካፒታሊ ዝምን ዲቃላ ራዕይ አንግቦ ፤ በአንዱም ውጤት ባለማም ጣቱ እጅግ ይጨንቀን ነበር ፤-

መ/ ሕዝቡ በዲቃላው ራዕይ ተወናብዶ አንዱንም ሳይጨብጥ አስካሁን ቢሠቃይም ፤ ሌላ አዲስ ሥርዓተ-መስተዳድር ከዘረኛነትና ሃይማኖታዊ ባላንጣነት ነፃ የሚያደርገውን መሠረት ሊጣልለት እንደሚገባ ንድፉን ያወጣነው ቀደም በዘመነ ደርግ ወቅት ነው ፡፡ " የጥቅል መንግሥት "

ሠ/ ኅብረተሰቡስ የሚመጣውን አዲስ ሥርዓተ መንግሥት ይቀበለው ይሆን ? ወይስ በዚያው በለመደው እንደተተራ መሰ ይኖራል ? የሚሉ በርካታ አስጨናቂ ሃሳቦች በውስጣ ችን ተመላልሰዋል ፡፡ ዛሬም እያስጨነቁን ነው !

ያም ቢሆን ያሰብነውና ዕቅዳችን ተቀባይነት ይኑረው አይኑረው ግድየለንም በሚል ሳይሆን በነዚህ ዙሪያ የሚመጣውን ማንኛውንም የፖለቲካ ሰው ወይም ድርጅትን በማወያየት በቂ ምላሽ በመስጠት / ቻሌንጅ / በማድረግ የሀገራችንን አዲስ ራዕይ በማስተዋወቁ ላይ ቁርጠኛ ሆነናል ፡፡

እንግዲህ በቁርጠኝነት ልንገልጽ የፈለግነውንና ፤ ከውስጣችን ልናስወግድ ያሰብነው ደካማ ጎናችንን በሚከተለው እነሆ እንላለን ፡፡

1/ የአውሮፓው ፕሮዳክት ዲሞክራሲ ካለን ንቃተ-ኅሊናና ከባ ኅልና እምነታችን ጋር የማይሄድ በመሆኑ ፤ ሊሄድም የማይ ችልና ያልቻለም በመሆኑ ፤ <u>የራሳችንን ዲሞክራሲ በራሳችን እንመሥርት ነው የመጀመሪያው ራዕያችን ፡፡</u>

2/ በጣም የጎዳንና ኋላቀር አድርጎን በብልጣ-ብልጥ ገዥዎች እጅ ላይ ጥሎን የዘመናት ውዳቂዎች ያደረገን ብሔር-ብሔ ረሰብ የተሰኘው አስተሳሰብ ስለሆነ ፤ በቁርጠኝነት ከላያችን አሽቀንጥረን በመጣል <u>በአንድ ሀገር ሕዝብነታችን ብቻ የጥ ቅል መንግሥትን መሠረት ልንጥል ይገባናል የሚል ነው 2ኛው ራዕያችን ፡፡</u>

3/ እኛ በዘርና ሃይማኖታዊ ባላንጣነት መከፋፈል ስሜት ውስጥ በመግባታችን ምክንያት ፤ ግለሰቦችና የእጅአዙር ባሪያ ገዥ ዎች ከጀርባችን ሆነው በሡሩብን አሻጥርና ፤ ወጥመዳቸው ውስጥ ወድቀንም ስለነበረ ፤ በየትውልዳችን ሁሉ መከራ ተቀ ባይ ሆነናል ፡፡ <u>አሁን ግን የባርያ ገዥዎች ኮድ ተሰብሯልና ዓይኖቻችንን እንግለጥ ነው 3ኛው ራዕይ ፡፡</u>

እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ ላስቀምጥ እወዳለሁ ፡፡ በሰሞኑ አንዳንድ ክስተቶች በተለይም ሃይማኖትን አንተርሶ ፤ አንድ ደካማ ግለሰብ የእስልምናን ሃይማኖት መጽሐፍ ማለትም /ቅዱስ ቁርዓን/ ን አቃጥላለሁ ብሎ ከመዛቱ ጋር በተያያዘ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ኦባማ ያሉትን ባጭሩ አስቀምጣለሁ ፡፡ " ይህ አሜሪካ ነው ! የሃይማኖት ወይም የዘር ልዩነት የሚካሄድበት አይደለም !! ማንኛውም ሃይማኖትና የሰው ዘር የሚኖርበት አገር ነው !! " ያሉት ታላቅ ምሳሌ በመሆኑ ለተስተውሎ ይረዳናል ፡፡ ሃሳባችን እኛ ባቀረብነው ራዕይ ሰው ሁሉ ማመን አለበት ፤ ወይም ሊቀበለው ይገባል ማለታችን አይደለም ፡፡ ነገር ግን ሰዎች ነንና ያሳለፍነውን የመከራ አገዛዝ ፤ ከዚህ አዲስ ራዕይ ጋር መዝነን የሚበጀንን እንምረጥ ለማለት ነው ፡፡ በዘርና ሃይማኖታዊ ባላንጣነት መንስኤ ያሳለፍነው ጊዜ ማለትም በከንቱ የተቃጠለው ጊዜ ለፍትሐዊ መንግሥት ካላበቃን ፤ ብሔር ብሔረሰብ የተሰኘውን አመለካከት እርግፍ አድርግን በመተዋችን ፍትሐዊ መን ግሥትን የሚያጎናጽፈን ከሆነ ፤ በየትኛው ላይ ብንቆይ መልካም እንደሆነ ኅሊ ናው ያለን ሁሉ እንድንመዝን ለማለት ነው ሃሳባችን ፡፡

<u>በመሠረቱ ባርነት ትግል አይጠይቅም</u> ! በአንፃሩም ትግልና መስዋዕትነትን
የሚጠይቀው ነፃነት ነው ! ባርነትን ለማስወገድና የባሪያ ገዥዎችን የአገዛዝ ኮድ
ለመጨረሻ ጊዜ ለመስበር ብሎም ሀገራችንና ሕዝባችን የዕውነተኛው ነፃነት ባለ
ቤት እንዲሆንና የራሱን ዲሞክራሲ በራሱ ፈጥሮ ለመኖር የጥቅል መንግሥት
አስተዳደራዊ ሥርዓት ምንም አማራጭ እንደሌለው በፍጹምነት ስለተማመንን
በት ነው ሕዝባችን ይፍረደው ብለን ንድፈ- ሃሳቡን ለማቅረብ የሞከርነው ፡፡
በኛ አመለካከት የዘር ድርጅት አንዱ ከሌላው ቅራኔ አለው ፤ የፖለቲካ ፓርቲ
ዎችም አንዳቸው ከሌላው ቅራኔ አላቸው ፤ " እኔ ካንተ እሻላለሁ አንተን ለዘለ
ዓለም አጥፍቼ የኔን ዘለዓለማዊነት እጠብቃለሁ ! " በሚል አንዱ ዘር ሌላውን
አንዱ ፓርቲ ሌላውን የሚያዳክምበት ሁኔታ በበርካታ ሀገሮች ተከስቷል ፡፡
ከሁሉም የሚገርመው የአንድ ሀገር ሕዝብ መሆናቸውን እስከ መዘንጋት መድረ
ሳቸው ነው ! በኛ ሀገር ዘርና ሃይማኖትን በማጋጨት የግል ጥቅማቸውን የሚያ
ነፈንፉ ቢበዙብንም ፤ ሕዝቡ ግን አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ ግፈኞችን አሳ
ፍሯል ፡፡ ሕዝባችን ያንን ውዥንብር ባይቋቋም ኖሮ እስካሁን ኢትዮጵያዊ የሚ
ባል ሕዝብ ባልኖረ ነበር ፡፡ አንደኛው ፓርቲ የሌላውን ፓርቲ ለጋብቻ የማይፈ
ላለጉበት ደረጃ ላይ የመገኘቱ ሁኔታ ፤ በሰለጠነውም ዓለም በእጅጉ የሚያሳስብ
ሆኖ እየታየ ነው !! በአንዳንድ ሀገረ መንግሥትም ውስጥ ካለመግባባት የተነሳ
በኮካ ኮላ ጠርሙስ እስከ መፈላለጥ መድረስ ፤ የግሩፑን ጥቅም ለመጠበቅ
ወይም በኔ የበላይነት አምነህ ኑር ከማለት የተለየ አስተሳሰብ እንዳልሆነ መገ
መት ይቻላል ፡፡ በዲሞክራሲ ሰም ያልተሠራ ግፍ የለም !! የሰው ልጆችን ሰብ
ዓዊ መብት ከመግፈፍ አንስቶ ማጭበርበሩና መዋሸቱ እየጎላ ነው የመጣው ፡፡
ዲሞክራሲ ማለት እንደዚያ ከሆነ ፤ በሰለጠነውስ ዓለም ያለው ዲሞክራሲ ለምን
ከኛ ዲሞክራሲ ጋር ተመሳሳይ አልሆነም ? ሲሉ የሚጠይቁት በርካታዎች
ናቸው ፡፡ የሕግ የበላይነት በሌለበት ሀገር ስለ ዲሞክራሲ ማውራት ፤ በምርጫ
ተሳትፌ ፓርላማ ከገባሁ " ዲሞክራሲ ከዚህ ያለፈ አይደለም !! " ብሎ መደን
ፋት እንደ ሀገራችን አባባል ላሞች ባልዋሉበት ......ይመስለናል ፡፡ ይህንን ሃሰት
ተቀብሎ የሚኖር ሕዝብ ደግሞ ነፃነትን ታግሎ ሊያገኛት ያልፈለገ ፤ ትግል
ለማይጠይቀው የ.....ሕይወት እጁን የሰጠ ነው ቢባል ቃለ አጋኖ አይሆንም ፡፡
በዚህም ተባለ በዚያ ለማንኛውም ፤-

መቼም ወቅቱ የለገሠንና በዲሞክራሲ ስም እንድንቀበለው የተገደድንበት
ኢ-ዲሞክራሲ ፤ ደርግ በነበረበትም ወቅት ዲሞክራሲ ተብሎ ኢ-ዲሞክራሲን ፤
አሁን ወያኔም ባለበት ወቅት ዲሞክራሲ እየተባለ ኢ-ዲሞክራሲን እየተቀበልን
መገኘታችን ታሪካዊ ሐቅ ነው ፡፡

እዚህ ላይ ድክመታችንንና ፤ የደረሰሰብንን ተጽዕኖ በማገናዘብ አንድ የጋራ
ሥራ እንሥራ ብለን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመሥርተው ነበር ፤ ግን
ፋይዳ አልነበራቸውም ፡፡ እንዲያውም ለነፃነት ተብሎ ሊካሄድ የሚገባውን የት
ግል ሥልት አቅጣጫ በመሳት ግራ ተጋብተው ፤ የትጥቅና ሰላማዊ ትግልን
መለየት ሳይችሉ ቀርተዋል ፡፡ ወላውለዋል ! አቋማቸውን ግልጽ ማድረግ ተስ
ኖአቸዋል !! የዚህ ትልቁ ምክንያት ምን ነበር ? 1/ አንዳንዶች ባርነት ትግል
እንደማይጠይቅ አውቀው ፤ ጌታዬ አንተ እንዳልህ ብለው ግላዊ ሰላማቸውን
በባርነቱ ውስጥ ጠብቀው መኖር ሲችሉ ፤ 2/ በሌላው ጎራ ያሉት ደግሞ በሀገ
ራዊ ጉዳይ ላይ አንድነት ሳይኖራቸው ፤ ዲሞክራሲን እናመጣለን እያሉ ፤ በከ
ወኑት አጉል መፍጨርጨር ለሽንፈት መዳረጋቸው ነው ፡፡ ትግሉ እንዳረጀ
የመኪና ሞተር ሲግልና ሲበርድ ፤ ሲነሣና ሲቆም ፤ ትውልዱንና ሀብተ ቅር
ሱን አስፈጅቶ ዛሬም ወያኔ ፈላጭ ቆራጭነቱን እንደተያያዘው ይገኛል ፡፡ ሌላም
የምናስተውለውና በምሳሌ የምናስቀምጠው ጉዳይ አለን ፡፡ ብዙሃኑ የኦሮሞው
ብሔር ታላቅ ነኝ ብሎ ነበር ፤ ግን በአንድ አናሳ ብሔር ነው ለሃያ ዓመታት
ሲጨፈጨፍ የኖረው ብንል ስህተት የሌለው ሐቅ ነው ፡፡ በዚህስ መሃል ማን
ተጠቀመ ? ቢባል መልሱ አስቸጋሪ አይደለም ፡፡ ለኦሮሞው ሕዝብ የነፃነት
ተስፋ ዳቦ ሲያስገምጡት የነበሩ የትግሉ ፈታውራሪዎች ብቻ ናቸው የተጠ
ቀሙት ፡፡ ይህንን ሐቅ ደብቀን በሁቱና ቱትሲ መሃል የደረሰው አደጋ በኛም
ላይ ሲፈጸም ማየት ያለማስተዋላቸው ውጤት ነበር ፡፡ አናሳውን ብሔር ካኩ
ራሩት ጌቶች የተነሳ ፤ እንዲሁም ባርነት ወይም ሆድ አደርነት ትግል እንደማ
ይጠይቅ ግንዛቤን በውስጣቸው ባሣደሩ አረሞች ምክንያት ፤ ወያኔው ሰማንያ
ሚሊዮኑን የተከበረ ሕዝብ ዝቅ አድርጎ በመመልከት " የትኛው ፈረንጅ ነው
የሚያድናችሁ ? " ሲል ጠይቆናል ባለጊዜው ወያኔ !! ይህም በአንዲት ሀገር
ውስጥ አንድነታችንን ያለመጠበቃችንም ውጤት ነበር ፡፡ በአንዲት ሀገር
ውስጥ አንዱ ዘር አብጦ ሌላውን ዘር መዋጥ እንደማይቻለው ያለመረዳታ
ችን ውጤት ነበር ፡፡ አንድ ዘር ልገንጠል ቢል ይህ የመገንጠሉ ጥያቄ ምን
ያስከትል ይሆን ? በሚል ተስተውሎ ያልተደረገበት ጥያቄ በመሆኑ ፤

ሀ-የሚገነጠለው ክልል ያለው ሪሶርስ ምን ያህል ነው ?

ለ- ምልዐተ-ሕዝቡ በዚህ ጉዳይ ይስማማል ወይ ?

ሐ-ግዛተ-ክልሉ ለሕዝቡ ይበቃዋል ወይስ አይበቃውም ?

መ-ነገ ሕዝቡ እየጨመረ ሲመጣስ የት ይደረሳል ?

ሠ-የግዛት ይገባኛል ጥያቄ ውስጥ ብንገባስ መተላለቅ አይመጣምን ? ወዘተ.....

ተብሎ ግንዛቤ ውስጥ ያለመግባት ውጤት ነው ። እዚያም ደረጃ ባለመደረሱና በስሜታዊነት ብቻ የቀረቡት የግንጠላ ጥያቄዎች ለዘመናት ሕዝባችንን አስጨፍጭፈው ሞራለ-ቢስ አድርገውት ፤ የዘር ትግሉንና የትግሉን አጋፋሪዎች ጨርሶ ውኑ ፋይዳቢሶች አድርጓቸዋል። ምናልባት ይህንን የሚጠራጠር ዛሬም ለውጥ በአዕምሮው ውስጥ የማያቃጭል ፤ ባርነትን አምኖ ከነፃነት ትግል የሸሸ ወይም ጥቂቱ የዘር ልክፍተኛ ብቻ ይመስለናል ።

# <u>የጥቅል መንግሥት አዲስ ሥርዓት</u>
# <u>ምን ይመስላል ?</u>

1/ የጥቅል መንግሥት አዲስ አስተዳደራዊ ዘዴ ፤ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የተቀበለ ፤ ከግለሰብ እስከ መላው ሕዝብ ምንም ዓይነት ልዩነት በሌለበት መልኩ ሰብዓዊ መብትን ፤ የሀገር ሉዓላዊነትን እንዲሁም ባኅልና ሃይማኖቱን ፤ የከበረ ቋንቋውን ፤ የተፈጥሮ ሀብቱን የሚያስከብር መንግሥት ነው ።

2/ በሁሉም ኢትዮጵያዊ የሁሉን መንግሥት ያማከለ ፤

3/ በጥቂት ግለሰቦች ጫንቃ ላይ በተጣለ ኃላፊነት ሀገርና ሕዝብ የሚማቅቁበት ሀብተ-ቅርስ የሚመዘበርበት ፤ የአንድን ጎሣ ወይም ብሔር የበላይነት የሚያሰፍኑበት ሌላውን ብሔርና ጎሣ ቀፍድደው የሚያሥሩበት ሥርዓት ሳይሆን ፤ ሁሉን በሁሉ ያቀፈ በማዕከላዊ መንግሥት የምንመራበት ሥርዓት ነው ።

4/ የጥቅል መንግሥቱ ሕገ-መንግሥት በሁሉ ኢትዮጵያዊ ድምጽ ተደግፎ በማዕከላዊ መንግሥት ፓርላማ የሚጸድቅ ሕገ- መንግሥት ይሆናል ። ይህም ሕገ-መንግሥት በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀ ሕዝባዊ ሕገ-መንግሥት ነው ። ማለትም የገዢዎች ሕገ-መንግሥት አይደለም ።

5/ ሥልጣነ መንግሥቱን ኢትዮጵያዊያን በሕዝብ ድምጽ ተመርጠው እስከ ተወሰነላቸው ጊዜ ድረስ የሚመሩት ይሆናል ።

6/ የጥቅል መንግሥቱ ለማንም አምባ-ገነን ዲክታተራዊ አገዛዝ በሩን የማይከፍት ፤ በምንም መልኩ ዲክታተር ሊገባበት የማይችል ፤ ምንም ዓይነት ቀዳዳ በር የሌለው በሕዝባዊ ሕገ-መንግሥት የሚመራ ሥርዓት ነው ።

7/ ሥልጣነ ገደብ የተወሰነበትና አሮጊው አመራር በአዲስ አመራር ጊዜውን ጠብቆ የሚተካበት ሥርዓት ነው !!

8/ የጥቅል መንግሥቱ ሥርዓት ቋሚና የማይናወጥ ፤ በየስድስት ዓመታቱ በሚደረግ ምርጫ ሕገ-መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት አሮጌው አመራር ለአዲሱ አመራር የሥልጣን ሽግግር ያሚያደርግበት ሥርዓት ነው ።

9/ ከፓርቲዎች ከዘር ድርጅትና ከመሳሰሉት ትርምስ ነፃ የሆነና ፤ በአንድ የጥቅል መንግሥት ማዕከላዊነት የሚመራ መንግሥት ነው ።

10/ እንደ ቀድሞዎቹ አገዛዞች ሕዝቡንና ሀገሪቱን ለአንድ ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር እንደ ፈለገህ ፍለጥ-ቁረጥ ተብሎ የሚሰጥና የግለሰብ ገናናነትን የምንቀበልበት ሳይሆን ፤ ለማዕከላዊ መንግሥት አመራር በሚመረጡ ሃላፊዎች እስከ ሥልጣነ ዘመኑ ማብቂያ የምንመራበት ሥርዓት ነው ።

11/ የጥቅል መንግሥቱ ከተለያዩ የዓለም መንግሥታት ጋር ያለውን ዓለም-አቀፋዊ የፖለቲካ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትን ለማጠናከር ፣ የሀገራችንና የሕዝባችንን ጥቅም ለማስጠበቅ ሕዝባዊውን ሕገ-መንግሥት መሠረት አድርጎ የሚንቀሳቀስ ነው ።

12/ ማንም ጠመንጃ አንጋች ፣ ማንም የፖለቲካ አዋቂ ነኝ በሚል ጀብደኛ አስተሳሰብ ካሁን በኋላ ኢትዮጵያን መቀለጃ ማድረግ አይፈቀድም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የዕውቀት መለኪያው በፈቀደለት መጠንና ፣ የሚኖርበት አካባቢ ሕዝብ በሚሰጠው ድጋፍ ወይም ድምጽ ለመራኄ መንግሥት አባልነት ብቃት ማግኘት ይችላል ።

# <u>እዚህ ላይ ግራ ላለመጋባት እናስተውል !!</u>

አሁን የምንገኝበት ጳፍንታም ሥርዓት በበርካታ ውስብስብ ዕምነቶች ውስጥ ያሠረን ከመሆኑ ባሻገር ፣ ተስተውሎና አዲስ ራዕይ የነፈገን አጥፊ ሥርዓት ነው ። ይህ የተጠመድንበት ሥርዓት ለአገዛዞች ከፍተኛ ጥቅም የሰጠውን ያህል ፣ የኛንም ጎልውና የሰው ልጅ ከሚጠብቀው በላይ ጎድቶታል ! አጎሣቁሎናል ! ከዓለማት የዕድገት እሽቅድድም ገትቶናል ! የኢኮኖሚ ጥገኛና ምጽዋተኞች አድርጎናል ! ቀናውንና አስታራቂውን መንገድ ከልሎን አርስ-በርስ ጥፋተኛ ነህ ጥፋተኛ ነሽ ተባብለን ፣ ዓይኖቻችንን ተደነቋቁለናል ! በተፈጥሮ ጸጋዋ የደለበች ሀገር ላይ ተቀምጠን ረሃብ-ድንቁርናና ስደትን ወዘተ...እያስተናገድን እንገኛለን ። እናም አሁን ያለን ዕድል አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ ብቻ ነው ። ይኸውም !-

ሀ. እንደነበርንበት ሥርዓት እየተተራመሱ ፣ ድኀነትን ፣ ድንቁርናን ስደትን ፣ የዓለማት ዝቃጭ ሆኖ በምጽዋት መኖርን ወዘተ.......... ማስተናገድና ፣ ያንንም ለትውልድ ማሸጋገር ፣ ወይም

ለ. ወደ አዲሱ ሥርዓት ውስጥ በቁርጠኝነት ገብቶ ሀገርንና ሰብዓዊ ክብርን ማስጠበቅ መቻል ነው ። እግዚአብሔር-አላህ ተስተውሎ ያለው አዕምሮ የሰጠው ሕዝብ ይህን መረዳት ያቅተዋል ብለን አንገምትም ። ምክንያቱም በሀገራችን የምሳሌ አባባል " ጨው ለራስህ ስትል ....... !! " ነውና ፣

ሐ. ከዚሁ ጋር በጥብቅ ሊስተዋል የሚገባ ሌላ ጉዳይም አለ ። ዘሬ ፣ ጎሣዬ ፣ ሃይማኖቴ የምንልበት አስተሳሰባችን ምን ያህል ጠባብ አድርጎን የወደፊቱን ዓለም እንዳናይ ራዕያችንን አጠፋብን ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ በሚከተለው አገላለጽ ለማስቀመጥ እንሞክራለን ፣- እንደ ምሳሌ !-

1/ አንድ ሰው ጎጃም ይወለዳል ፣ ጎጃም ውስጥ ተወልዶ አድጎና ጎልምሶ አርጅቶ ደክሞ ይሞታል ። ይህ ሰው ኢትዮጵያዊ ነው ! በኢትዮጵያዊነቱም ያምናል! የባሌውን አርሲውን ፣ አፋር ጋምቤላውን ፣ ሐረርጌውን ወለጋውን ወዘተ... ሁሉንም እንደ ጎጃሙ ሰው እንውሰዳቸው ፣ የጎጃሙ ሰው በኢትዮጵያዊነቱ በሰንድቅ ዓላማው በኢትየዮጵያ ሕዝብም እያመነ ፣ ነገር ግን ኢትዮጵያን ዞሮ አላያትም ፣ ትዳር በመመሥረት ፣ ልጆች በማፍራት በግብርና በንግድ ሥራ ሀብት በማፍራት ተዘዋውሮ አልተጠቀመባትም ። ምክንያቱም ከፋፍለህ ግዛው ዓይኖቹን ስለከለሉበት ነው ።

2/ ይህ በአንድ ክልል ተወስኖ የመኖሩ ሁኔታና አፈፃጸሙ ለማን ጠቀመ ? ምንን አስከተለ ብለን ዳሰሳ ስናደርግ ያገኘነው ምላሽ ፣-

ሀ / ገዥዎች በከፋፍለህ ግዛው ማደናቆራቸውን !!

ለ / ጎጥን አጠናክረን እንዳንተያይ እንዳንዋደድ ፣ እርስ በርስ የጥላቻ ቂም እንድንያያዝ ፣ በሀገራችን ውስጥ ተዘዋውረን እንዳንጠቀም ነው ያደረጉን ። ዛሬም ከዚያ ጭንብስ አልወጣንምና ከፋፍለህ ግዛው ይቀጥል ወይስ ይጥፋ ? !!

ሐ/ በዚህ የከፋፍለህ ግዛው ቀዳዳ ሰብረው በመግባት ቅኝ ገዥዎችና ሥልጣን ቋማጭ ፣ ዲክታተርና ጨፍጫፊ ገዥዎች ለሕዝብ ልዕልና ሳይሆን ለግል ጥቅማቸው በመቆም ፍጹም በአጎጉራችን ሊሰፍን ያልቻለውን የአውሮፓን ፕሮዳክት ዲሞክራሲ እናሰፍናለን እያሉ ፍዳችንን እያበሉን ይገኛሉ

መ/ ዛሬ በዓለማችን የምናያቸው የዲሞክራሲ ሂደቶች አንድ-
ወጥ እንዳልሆኑና ዲሞክራሲው በዝግመት ከመጓዝ አልፎ
ገና አመርቂ ውጤት ላይ እንዳልተደረሰ ግልጽ ነው። ያም
ቢሆን ከፍሬ አልባው የተውሶ ዲሞክራሲ ይልቅ ፤ የራስን
ዲሞክራሲ የራስን ባኅል-ልማድና ሃይማኖት በሚጠብቅ
መልኩ መፍጠር ብስለት እንጂ ደካማነት አይመስለንም ።

ሠ/ በርግጥ በዚህ ውዥንብር ውስጥ ሆነን ነገ ዲሞክራሲ ይሰፍ
ናል ብለን ጓጉተናል ። ስለ ዲሞክራሲ ብቻ ሳይሆን ሀገርና
ሕዝብ ማለት ምን ማለት ነው ? ተብሎ ቢጠየቅ በቂ መልስ
ለማይሰጡ ስግብግቦች መሪ ይሆኑናል ብለን የጮህንላቸው፤
የተጠየቀውን መስዋዕትነት ሁሉ የከፈልንላቸው እኛ ፍት
ሐዊ መንግሥት ይመጣልን ይሆናል ፤ ሰላም አግኝተን ሀገራ
ችን ታድጋለች ፤ ልጆቻችንን በመልካም ሁኔታ እናሳድግ
ይሆናል ብለን በመጓጓታችን እንጂ በጅል አስተሳሰብ ተነድ
ተን አልነበረም ። ያም ቢሆን የተፈጸመብንን በደል በእምቢ
ተኝነት ገልጸን በዳዮችን ለፍርድ ማቅረብ ያልቻልነው ከላይ
በፊደል ሀ እና ለ ከተገለጹት ሁኔታዎች አኳያ የተፈጸመ
ብን ክፉፍለህ ግዛው ስላነቀን ነው ።

በሌላም ምሳሌ አውሮፓን እንመልከት ፤ በተለያየ የመንግሥታት ስያሜ
ብቻ ሳይሆን ፤ እንደ አንድ የአውሮፓ መንግሥት በአንድ ቤት ጣራ ሥር
መኖራቸው ማንንም ሊያስደንቅ ይችላል ። እኛን ስንመለከት ደግሞ እንኳንስ
በአኅጉር ደረጃ ልንስማማ ቀርቶ ፤ መልካችን ፤ ደማችን ፤ ትውልዳችን ዘራችን
ተደባልቆ ፤ በባኅላችን በታሪካችን አንድ ነን እያልን በአንዲት ኢትዮጵያችን ፤
የራሳችን ቤት ነች ብለን በምናምንባት ፤ የቤታችን ጣራ ሥር በአንድነታችን
ተግባብተን መኖር አልቻልንም !!! በዚህ የአመለካከት ጉዳይ ቆም ብለን ራሳች
ንን እንድንጠይቅ ወቅቱ ግድ እንደሚለንም ሊስተዋል ይገባል ። ይህን ደከማ
ጎናችንን በተመለከተ ለምን እንዲህ ይደረጋል ብሎ ከሚነሳው ይልቅ ፤ ለግል
ጥቅሙ ሲል ሕዝብን ከሕዝብ እያጋጨ የሚኖር ሰብዓዊነት የማይሰማው ዲክታ
ተር ተፈልፍሎብን በየጊዜያቱ ተቀብለን ማስተናገዱ ግድ ሆኖብን ኖረናል ።

ታዲያ ዛሬ አዲስ መንገድ ለመቀየስና የትውልዱ ሥቃይ እንዲያበቃ ማድረግ
አንችልምን ? በአገዛዞች ምክንያት ምንም ፋይዳ በሌለው ሁኔታ ትናንት ስን
ፋጭ የነበርን ወገኖች ዛሬ ይቅር ለእግዜር ብለንና በአንድነታችን ተማምነን ፤
ለኛ አሁን ለምንገኘው ትውልድና ለቀጣዩም ትውልድ የሚበጅ አዲስ ሥርዓት
ለመፍጠር አንችልምን ? ይህንንስ ለማድረግ ከልካይ አለብን ? ስለዚህ የጥ
ቅል መንግሥት አዲስ ሥርዓት ችግራችንን በፍጹምነት የሚቀርፍ ፤ ባኅላችንን
ዕምነታችንን ባመለካተ ሁኔታ የራሳችንን ዲሞክራሲ በራሳችን እንድንፈጥር
የሚያደርገን በመሆኑ ፤ ከነበርንበት ውዥንብር ራሳችንን ለማውጣትና ፍት
ሓዊ መንግሥት እንዲኖረን ፤ ሁላችንም የአዕምሮ ለውጥ ማድረግ ይጠበቅብ
ናልና እናስተውል ።

አውሮፓ ዘልቀው ስለ ዲሞክራሲ ተምረው ወደ ሀገራቸው የተመለሱ ወይም
በዚያው ሰለጠነ በተባለው ዓለም ውስጥ በመኖር ላይ የሚገኙ የዲሞክራሲው ባላ
ባቶች የዲሞክራሲን ጥቅም በመግለፃቸው ላይ ምንም ተቃውሞ የለንም ። በመ
ሆኑም ዲሞክራሲውን የሚተነትኑለት ሕዝብና ዲሞከራሲውን አንድ ቴክኒሽያን
እንደሚገጣጥመው ሞተር መገጣጠሙ ላይ ትክክል አልመጣላቸውም !! ሕዝቡ
ንና ዲሞክራሲውን አላገናኙትም ለማለት ነው ባጭሩ !! በመሠረቱ ሕዝቡን ከአ
ውሮፓው ዲሞክራሲ ጋር ለማዋሃድ ፤

ሀ/ ለሕዝቡ ንቃተ-ኅሊና ደረጃ ግምት ሊሰጠው ይገባ ነበር ፤ ማለትም የዲሞ
ክራሲውን ባኅሪያት ሊረዳና ሊቀበል የሚያስችለው አዕምሯዊ ብቃት ይኖ
ረዋል ? ወይም አለው ወይ ? መባል ነበረበት ። ግን እንደዚያ አልተባለ
ምና ለ40 ዓመታት የተደሰኮረው ዲሞክራሲና ደስኳሪዎቹ ከንቱ ሆነው
ቀሩ ቢባል ያልተዛባ ሐቅ ነው ። የማያጠግብ እንጀራ በምጣዱ ላይ......
እና ይህንን ሐቅ የዲሞክራሲው ባላባቶችም ያምናሉ ፤ ባያምኑ እንኳን
ተግባራቸው ድንጋይ ላይ ውሃ እንደማፍሰስ ነውና ይጸጽታቸው ይሆናል!
በሚለው ላይ ዕምነታችን ጽኑ ነው ።

ለ/ ከዲሞክራሲው በፊት ሕዝቡን በአስተሳሰቡ እንዲነቃ ፤ ከቀድሞው ያላደራጁት ፤ ያላስተማሩት ሲሆን ፤ የሶሻሊስት አብዮትን ፤ የነፃ ገበያ ባለዲሞክራሲዎችን የካፒታሊዝም ፈለግ መከተል አለብህ በሚል ዲቃላ ራዕይ አምጥተው በአዕምሮው ውስጥ ከመሰግሰጋቸው፤ ወይም ከማጨቃቸው በስተቀር ግማሽ መንገድ ከሄዱ በኋላ እንኳ ፤ ወደኋላ ተመልሰው ሕዝቡን እናንቃ አላሉም !! ብቻ ዲሞክራሲን ተቀበል ! በዲሞክራሲ ስም የሚመጣብህን የኢ-ዲሞክራሲ አፈናውን ! የሰብዓዊ መብት ረገጣውን ተቀበል እያሉ አሁን የምንገኝበት መቅ ሕይወት ውስጥ ጥለውናል :: ነገ ልጆቻችን ይህንኑ መከራ እንዲቀበሉ ድግሡ ተደግሶ ተቀምጦላቸዋል !!! ታዲያ ይህን መሰሉ ግፍ የማይቆጨውና፤ ከኋላ ቀር አስተሳሰቡ ወጥቶ መልካሙን ራዕይ የማይመለከት ፤ የአዲሰ ሥርዓት ለውጥ በአዕምሮው የማያቃጭል የትኛው የኢትዮጵያ ልጅ ነው ?

ሐ/ ይህ በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ሀገሪቱንና ሕዝቦቿን ፤ ታሪክ ሠሪ ጥበበኞቿን አስበልቶ ፤ የአንድን ጎሣ የበላይነት አጎልብቶ ብዙሃኑን ከከርሡ ምድር ሲደባልቅ ፤ ዘሩ ሃይማኖቱ ወይም የሚፈልገው ዕምነቱ ያለምንም ተጽዕኖ ጸንቶ የሚኖርበትን አዲስ ሥርዓተ መንግሥት የማይፈልግና ለውጥ በአዕምሮው የማያቃጭል የትኛው የኢትዮጵያ ልጅ ነው ???

መ/ ከላይ ያልነውን ስንገልጽ የማንንም መብት ለመንካት ፤ ማንንም ለማስገደድ ሳይሆን ፤ ሰዎች ነንና እንደ ሰው እናስብ ለማለት ብቻ ነው :: ትግል የማይፈጀውን ባርነት ተቀብሎና አሜን ብሎ መቀመጥ የማንኛውም ግለሰብ መብት ቢሆንም ፤ ነገ ለልጁ የሚያወርሰው የራሱ ውዳቂ ታሪክ ነውና አስቀድመን እናውቀዋለን ::

ስለዚህ ከኋላ ቀሩ የዘርና ሃይማኖታዊ ባላንጣነት ነፃ የሚያወጣንን የጥቅል መንግሥትን አዲስ አስተዳደራዊ ሥርዓት የሚያመለክተውን መሪ ራዕይና ፤ የሕገ-መንግሥቱን ረቂቅ ሃሳብ ለሞዴል ያቀረብነው በመሆኑ፤ ነገሮችን በጥልቅ ተመልክታችሁ ነፃ ውይይት በማድረግ ሀገራችንን ከወደቀችበት ለማንሣት ሕዝባችን ከተጠመደበት ፋሽስታዊ አገዛዝ ነፃ ወጥቶ የሠላም አየር እንዲተነፍስ ፤ የየበኩላችንን ጥረት እንድናደርግ እንጠይቃለን ::

<u>ማስጠንቀቂያ ፤-</u>

ወያኔና የወያኔ ደጋፊ ኃይላት ሀገር የመበዝበዝ ፤ ሕዝብ የማራቆት የወደፊት ኢትዮጵያዊነትን ራዕይ ፈጽሞ ለማጥፋት ፤ የጀመሩት ሤራ እንዲሰናከልባቸው ስለማይፈልጉ ፤ በተለያየ ሜዲያ እስከ ዛሬ ሕዝባችንን የፖለቲ ካፓርቲዎችን ፤ የዘር ድርጅቶችንና ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለውን ሁሉ ግራ እያጋቡ መቆየታቸው ግልጽ ነው :: አሁንም በኛ ድክመት ይበልጥ ሊዝናኑብን በመቻላቸው ማንአለብኝነት ደረጃ ላይ ደርሰዋል :: ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት በየኤምባሲዎቻቸው አፍራሽ ኃይሎች አማካይነት በየፓልቶኩ ተሰግስገው ግራ ማጋባቱን ቀጥለውበታል :: እንዲህ ዓይነቱን ሕዝባዊ ውይይት መስማት ስለማይፈልጉ ፤ሕዝባችን ለውጤት እንዳይበቃ ሲባል የወያኔ መንጋዎች በተለያየ ጊዜና በየሜዲያዎቹ ሲፈጽሙ የነበረውን ሸር ታውቁታላችሁ :: አሁንም ይህ ዓይነቱን ሕዝባዊ ውይይት በንቃት እንዳንወያይበት መሰናክል መፍጠራቸው ስለማይቀር ለነፃነትህ የቆምህ ኢትዮጵያዊ የሀገርህን ጉዳይ በጤናማ መንፈስ መወያየትና አጥፊህን ወጊድ ማለት ይጠበቅብሃል :: በዚህች ሀገራችን መውደቅ ምክንያት የደረሰብን መከራው ያንገፈገፋችሁ ሁሉ ፤ የተለመደው ቅስፈታዊ የጠላቶቻችን ተልዕኮ እያደገ እንዳይመጣ የምትፈልጉ ወገኖች ሁሉ ፤ ሀገራችሁን አስከብራችሁ መከበርና ለቀጣዩ ትውልድ የተከበረች ሀገር ማስረከብ የምትፈልጉ ሁሉ ፤ ሕዝባችንንና ሀገራችንን ከጭራቆቹ መንጋጋ እናላቅቅ ዘንድ በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን ::

ይህ ጥሪ በዕውነት ለዚህች ሀገር ቆመናል የሚሉትን የፖለቲካ ድርጅቶችና በሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል ነፃነቴን እፈልጋታለሁ የሚሉትን ኢትዮጵያዊያንን የሚጋብዝ በመሆኑ ፤ አንድ ታላቅ ሕዝባዊ መወያያ በጋራ አዘጋጅተን ስለ አዲሱ የጥቅል መንግሥት ዓላማናተግባር ፤ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ስለተነደፈው ሕዝባዊ ሕገ-መንግሥት ረቂቅ ሃሳብ እንድንወያይና ለመፍትሔም እንድንበቃ ያላችሁን አስተያየት ይህ ሃሳብ በተገለጸበት ድኅረ-ገጽ ላይ ታስቀምጡ ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን ::

የኢትዮጵያ አፋኞች በጀግኖቿ አንድነት ይሰበራሉ !

ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች !!